የእስራኤል መንግሥት
የሲቪል አገልግሎት ኮሚሽን
የሴቶች ማስቀደሚያና ተዋጎዶ ክፍል


# ወሲባዊ ትንኰሳን መከላከል

## ዋና ዋናዎቹ መመሪያዎች

ይህ አስገዳጅ የሆነው የዕብራይስጥ የሕግ ቅጂ ወሲባዊ ትንኰሳን ለመከላከል በተደነገገው የ1988 ዓ.ም. ሕግና በተሻሻለው የመንግሥታዊ አገልግሎት ደንብ ውስጥ ወጥቷል። ይህ ማስታወቂያ የወጣው በሕጐቹና ደንቦቹ ምትክ አይደለም። ሕጐቹንና ደንቦቹን በሙሉ በሚከተለው መንግሥታዊ ድረ ገጽ ላይ ማየትና ማንበብ ይቻላል።
http:// www.civil-service.gov.il/Civil-Service/TopNAvHe/Units/Woman/LawsTakanot

አስገዳጅ የሆነው የሕግ ቅጂና መመሪያው የዕብራይስጡ ቅጂ ብቻ ነው።

ማንኛውም በአንስታይ ጾታ የተጻፈው ተባእታይ ጾታን በተባእታይ ጾታ የተጻፈው ደግሞ አንስታይ ጾታን ይመለከታል።

**ወሲባዊ ትንኮሳና ከእሱ ጋር የተያያዙ ድርጊቶች የሰውን መብት፣ ነጻነቱን፣ ግላዊ መብትንና ጾታዊ እኩልነትን የሚነካ ነው። ስለሆነም እነዚህ ትንኰሳዎች በማንኛውም ቦታ ሆነ በማንኛውም መንገድ በሕግ መሠረት ክልክል ናቸው።**

### ከፍተኛ ቅጣት፡

ወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ትንኮሳውን ማቀድ የሚያስከትለው ከፍተኛ ቅጣት ከ2 እስከ 4 ዓመት እስር ነው።

### ሕጉ ማንን ይመለከታል?

ወሲባዊ ትንኮሳው ወይም የትንኮሳው ዕቅድ የሚፈጸመው በወንዶች ወይም በሴቶች አማካይነት ሊሆን ይችላል። ድርጊቱ የሚፈጸመው ደግሞ በወንዶች ወይም በሴቶች ላይ ሊሆን ይችላል።

### የተከለከሉ ድርጊቶች፡

ፍላጐት ለማያሳይ ግለሰብ ወሲባዊ ጥያቄ ማቅረብ (በበላይና በበታች ሠራተኛ መካከል ያለውን ግንኙነት በመጠቀም)፣ በሰው ወሲባዊ ድርጊት ወይም ዝንባሌው ላይ ተመሥርቶ ግለሰቡን ማዋረድ እንደወሲባዊ ትንኮሳ ይቆጠራሉ። አንድ ድርጊት እንደወሲባዊ ትንኮሳ የሚቆጠረው ወሲባዊ ዝንባሌ ካለው ነው። (ስለሆነም ለምሳሌ ቡና መጋበዝ ወይም ስለጸጉር መስተካከል/አቆራረጥ አስተያየት መስጠት ትንኮሳዎች አይደሉም።) እንደዚሁም ድርጊቶቹ ከወሲባዊ ድርጊት ጋር የተያያዙ መሆን የለባቸውም። (ለምሳሌ የሚያዋርዱ ድርጊቶች፣ ማስፈራሪያዎች፣ ወዘተ. እንደትንኮሳ ሊቆጠሩ ይችላሉ።)

### የሚከተሉት ድርጊቶች አንድ ጊዜ እንኳን የተፈጸሙ ከሆኑ ክልክል ናቸው

- ወሲባዊ ድርጊትን በማስፈራራት ለመፈጸም መሞከር
- የተወገዘ ድርጊት (ግለሰቡ ሳይስማማ ለማዋረድ ሆነ ወሲባዊ ፍላጐቱን ለማነሣሣት የሚፈጸም ድርጊት)። ለአንድ ግለሰብ ጾታውን ወይም ወሲባዊ ዝንባሌውን በተመለከተ የሚያዋርድ አስተያየት መስጠት

### የሚከተሉት ድርጊቶች በመደጋገም የተፈጸሙ ከሆኑ ከሆኑ ክልክል ናቸው

- በግለሰብ ወሲባዊነት ላይ ያተኮሩ ተደጋጋሚ አስተያየቶች፣ ወሲባዊ መልክ ያላቸው ተደጋጋሚ ጥያቄዎች
- አስተያየት የቀረበለት ግለሰብ ትንኮሳውን ለፈጸመው ሰው እምቢተኛነቱን በግልጽ ካሳየ (በንግግር ሆነ በአኳኋኑ)
- አስተያየት የቀረበለት ግለሰብ ትንኮሳውን ለፈጸመው ሰው እምቢተኛነቱን በግልጽ እያሳየ ተንኳሹ ሰው በድርጊቱ ከገፋበት

**ድርጊቶቹ የሚፈጸሙት ወይም አስተያየቱ የሚሰጠው እኩል የኃይል ደረጃ በሌላቸው ሰዎች መካከል ከሆነ** (ለምሳሌ በሠራተኛና አሠሪ መካከል ከሆነ)፣ አስተያየት የቀረበለት ግለሰብ እምቢተኛነቱን እንኳን ባያሳይ **ተደጋጋሚ አስተያየቶቹ ራሳቸው ወንጀል ናቸው፣**

### የተከለከሉ ሴራዎች፡

በወሲብ ትንኰሳ ላይ ክስ የመሠረተ ሰውን መተናኰል/መጉዳት።

### ወሲባዊ ትንኰሳ ተብለው የማይታሰቡ ድርጊቶች፡

በጋራ ስምምነት፣ በጥሩ መንፈስና በነጻነት የሚደረግ መፈቃቀድ ትንኰሳ ተደርጐ አይታሰብም።

### አቤቱታ ለማን ማቅረብ ይቻላል?

አቤቱታ አቅራቢዋ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ሁሉንም ወይም ከፊሉን መምረጥ ትችላለች።

- በመንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ወይም በሆስፒታል ውስጥ ለሴቶች መብት ተወካይ ለሆነ ግለሰብ ማመልከት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ በሲቪል አገልግሎት ኮሚሽን ውስጥ የሴቶች ማስቀደሚያና ተዋጎዶ ክፍል ተወካይ ለሆኑት ግለሰብ ወይም በሲቪል አገልግሎት ውስጥ ለዲሲፒሊን ክፍል ማመልከት ይቻላል።
- አቤቱታውን ለፖሊስም ማቅረብ ይቻላል (ለወንጀል ፍርድ ክፍል)
- ያለምንም የጉዳት ማረጋገጫ እስከ 50 ሺህ ሼቄል ካሳ እንዲከፈል ክስ ማቅረብ ይቻላል። እንደዚሁም ትንኮሳው የተፈጸመው በሥራ ቦታ ከሆነ ለተረጋገጡ ጉዳቶች (በሲቪል ክስ) ተጨማሪ የካሳ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል።


**ይህ ሰነድ ወደአማርኛ የተተረጐመው በአዲስ ገቢዎች ማስተናገጃ መሥሪያ ቤት አማካይነት ነው።**